በስመ አብ ወወልድ

ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ

አሜን።

# ስለ ቅዱሳን የምናምነው ምንድር ነው?

**መምህር፡- ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ**

**E-mail:** kesisolomon4@gmail.com

***ቦታ፦*** **ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ**

**በየሳምንቱ ረቡዕ ምሽት** ከ12፡30 – 1፡30

**ሐምሌ ፲፬ ቀን ፳፻፪ ዓ.ም.**

# መግቢያ

- በኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን ቅዱሳን ሰዎችን እናከብራለን፣ ከፍ እናደርጋቸዋለን እንዲሁም ምሕረትን፣ ይቅርታን ከአምላካችን ከእግዚአብሔር ይለምኑልን ዘንድ ወደ ነርሱ እንጸልያለን፡፡
- እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምንና ቅዱሳንን ማክበር ነፍሳችን የምትታመንበት የኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ሃይማኖታችን ቁልፍ አስተምሕሮ ነው፡፡
- ስለዚህ ዛሬ እንደ መግቢያ የምንማረው ቅዱሳንን ስለምን እንደምናከብር… ነው፡፡

***ቅዱሳን እግዚአብሔር ሰውን ለማዳን የሠራውን ሥራ የምናደንቅባቸው ናቸው***

- ቅዱሳንን በማክበር እግዚአብሔር ሰውን ለማዳን የሠራውንና የፈጸመውን ሥራውን እናደንቅበታለን፡፡
- ቅዱሳን ያደረጉትን መንፈሳዊ ተጋድሎና የተቀዳጁትንም ድል በማድነቅ ቤተ ክርስቲያን በርግጥም የእግዚአብሔርን የማዳን ሥራ ታከብራለች፣ በቅዱሳኑ በተፈጸመው የማዳን ሥራ መንፈስቅዱስ ያከናወነላቸውንና ወደፊትም የቤተ ክርስቲያን ተከታዮች ሁሉ ይደርሱበት ዘንድ ስለሚጋደሉለት ግባቸው እናደንቃለን፡፡
- እግዚአብሔር በቅዱሳኑ የተነሳ ሰውነታችንን እንዴት አክብሮታል?
- ቅዱሳን የሚደምቁት በአምላካችን ብርሃን ነው፣ በክብሩ ተቀድሰዋል፣ የሰውነታቸውንና የነፍሳቸውን የኃጢአት እድፍ በርሱ በማንጻት ተውበዋል፣ ሙስና መበስበስ በሌለበት በርሱ ከነውር ሁሉ ነጽተዋል፡፡
- ተፈጥሮአችንን ያከበረው፣ ነጻ ያወጣን፣ እኛንም ያከበረን እግዚአብሔር አምላካችን የተመሰገነ ይሁን፡፡
- ቅዱሳን ድል ብናደርግ በእግዚአብሔር የምንደርስበትን የመጨረሻ የተመረጠ ዕድል ማሳያ ናቸው፡፡
- ድል ባደረጉበት ሕይወታቸው ምሳሌነት የመለኮት ባሕርይ ተካፋዮች ወደ መሆን ስለመድረስ ያስተምሩናል፡፡ ‹‹ስለ ክፉ ምኞት በዓለም ካለው ጥፋት አምልጣችሁ ከመለኮት ባሕርይ ተካፋዮች በተስፋ ቃል እንድትሆኑ፥ በእነዚያ ክብርና በጎነት የተከበረና እጅግ ታላቅ የሆነ ተስፋን ሰጠን፡፡›› ***ካል ጴጥ 1፡4፡፡***

# መግቢያ

## *የተቀደሰ ሰው ማለት ምን ማለት ነው?*

- የተቀደሰ ሰው የእግዚአብሔርን መልካምነት የበለጠ ማራኪና ተደናቂ የሚያደርግ ነው፡፡
- ቅዱሳን ይቅርታን ያገኙ ኃጢአተኞች ሲሆኑ እግዚአብሔር ባደረገላቸው ይቅርታም ሕይወታቸውን የሚመሩ ናቸው፡፡
- ቅዱሳን ሌሎች ሰዎች በእግዚአብሔር እምነት እንዲኖራቸው **በቀላሉ** በሕይወታቸው የሚያስተምሩ ትምህርት ቤቶች ናቸው፡፡
- ቅዱሳን ሰዎች ማለት የክርስቶስን ብርሃን በውስጣቸው እንዲበራ ፈቃደኞች የሆኑ ክርስቲያኖች ማለት ነው፡፡
- ከቅዱሳን ሥዕላት ፊት ለፊት መብራት (ሻማ) የምናበራው ያለ ብርሃኑ - አየሱስ ክርስቶስ ቅዱሳን ምንም እንደሆኑ ለማስረዳት ነው፡፡ ብርሃኑ ኢየሱስ ክርስቶስ በሰውነታቸው ሲበራ ነው ሕያዋንና ለዓለምም አስደናቂ ይሆናሉ፡፡ ‹‹ በእኔ የሚያምን ሁሉ በጨለማ እንዳይኖር እኔ ብርሃን ሆኜ ወደ ዓለም መጥቻለሁ፡፡›› *ዮሐ 12፡46፡፡*
- በዚህ ዓለም ቅዱሳን እንደሆኑ የሚያስቡ ኃጢአተኞችና ኃጢተኞችን መሆናቸውን የሚያውቁ ሁለት ዓይነት ሰዎች ይኖራሉ፡፡
- በኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔርን ብርሃን ያዩ ቅዱሳን በመንፈሳዊ ሕይወት ታላቅ ደረጃ ላይ ስለመድረሳቸው ፈጽመው ተናግረው አያውቁም፡፡
- ቅዱሳን ወደ ወዲያው ዓለም ሲወሰዱ በሦስት ነገሮች ይደነቃሉ፡፡ እነዚህም አስቀድሞ ያላሰቡአቸው ወይም ያልጠበቁአቸው ብዙዎች በእረፍት ሥፍራ በመገኘታቸው፣ እናገኛቸዋለን ብለው የጠበቁአቸው አንዳንዶች በእረፍት ሥፍራ ባለመገኘታቸውና ራሳቸው በእረፍት ሥፍራ በመገኘታቸው የሚከሰት መደነቅ ነው፡፡
- ቅዱሳን በሌላው ኃጢአት ውስጥ ራሳቸውን ይመለከታሉ፡፡ ቅዱሳን ክርስቶስ የሚኖርባቸው ማኅደሩ፣ ለክርስቶስም ሕይወታቸውን ከፍተው የሰጡ ሆነው እግዚአብሔር እንደፈቀደው ወይም እንደሚወደው ሆነው የሚመሩ ናቸው፡፡

# መግቢያ

## ***የተቀደሰ ሰው ማለት ምን ማለት ነው?***

- የእግዚአብሔር ቅዱሳን ልብሳቸውን አስረዝመው የሚያስመስሉ አይደሉም፡፡ በሥራቸው ሁሉ እንደ ተራ ሰው ተሰማርተው የሚገኙ፣ ግብራቸውን የሚከፍሉ፣ ከሰውም ጋር የሚነጋገሩ እግዚአብሔር የሚናገረውን ቃሉን የሚፈጽሙና የሚጠብቁ ናቸው፡፡
- የእግዚአብሔር ቅዱሳን የሚፈሩ ቢሆኑም ‹‹አትፍሩ›› ያላቸውን የእግዚአብሔርን ቃል ኪዳን ተስፋ ያደርጋሉ፡፡
- የእግዚአብሔር ቅዱሳን ደካሞች እንደሆኑ ቢያውቁም በእግዚአብሔር ኃይል ይመካሉ፡፡ ‹‹ የሚመካ ግን በጌታ ይመካ፡፡» *ካል ቆሮ 10፡17* እንደተባለ፡፡
- *ሁሉን እንደያዙ አያስቡም ወደ ግባቸው ለመድረስ በርትተው ይሠራሉ እንጂ፡፡ « ወንድሞች ሆይ፥ እኔ ገና እንዳልያዝሁት እቈጥራለሁ፤ ነገር ግን አንድ ነገር አደርጋለሁ፤ በኋላዬ ያለውን እየረሳሁ በፊቴ ያለውን ለመያዝ እዘረጋለሁ፥ በክርስቶስ ኢየሱስ ከፍ ከፍ ያለውን የእግዚአብሔርን መጥራት ዋጋ እንዳገኝ ምልክትን እፈጥናለሁ፡፡»* ***ፊል 3፡13-14፡፡***
- ቅዱሳን ሰዎች እግዚአብሔርን ለማያምኑ ሰዎች የማሳመኛ መልሶች ናቸው፡፡
- ቅዱሳን ሰዎች የክርስትና ሕይወት ምንነት ማሳያ ምሳሌዎች ናቸው፡፡
- ቅዱሳን እግዚአብሔርንና ባልንጀራቸውን የሚወድዱ ናቸው፡፡ እግዚአብሔርን በፍጹም ነፍስ፣ ኃይልና በፍጹም ልብ በመውደድ ለባልንጀራቸውም ሕይወታቸውን የሚሰጡ ናቸው፡፡
- ቅዱሳን በግሪክ ቋንቋ «ሀግዮስ» ተብሎ ከሚታወቅ ቃል ተወስዶ እንደ ሌሎቹ ያልሆኑ የተለዩ የሚለውን ትርጉም ይይዛል፡፡
- ቅዱሳን በዚህ ዓለም ከሚኖሩ ሰዎች ይለያሉ፡፡ ለእግዚአብሔር ፈቃድ የሚታዘዙና ደስ የሚያሰኘውንም የሚፈጽሙ ናቸው፡፡
- ቅዱሳን የክርስቶስ አካል የሆነች የቤተ ክርስቲያን አባላት ሆነው እግዚአብሔር ሥራውን በዓለም የሚያከናውንበት የእግዚአብሔር እጆች ናቸው፡፡
- ቅዱሳን ካረፉም በኋላ በሰማይ ሆነው ለእኛ በመጸለይ የማማለድን የፍቅር ሥራ የሚፈጽሙ ናቸው፡፡

# መግቢያ

## *የተቀደሰ ሰው ማለት ምን ማለት ነው?*

- አንድ የዓይን ሐኪም ዓይንዋን በቀዶ ጥገና ያበራላት አንዲት ሴት ከሆስፒታሉ ስትወጣ የእግዚአብሔርን ሥራ ወይም እግዚአብሔርን በርሱ አይቼበታለሁ ስትል ‹‹እግዚአብሔር ደህና ሁን›› አለችው የሚል አባባል አለ፡፡ ቅዱሳን ዛሬ ላለው ዓለም የእግዚአብሔር ማሳያዎች ናቸው፡፡
- ‹‹ በሚድኑቱና በሚጠፉቱ ዘንድ ለእግዚአብሔር የክርስቶስ መዓዛ ነንና፤ ለእነዚህ ለሞት የሚሆን የሞት ሽታ ለእነዚያም ለሕይወት የሚሆን የሕይወት ሽታ ነን፡፡ ለዚህም ነገር የሚበቃ ማን ነው? የእግዚአብሔርን ቃል ቀላቅለው እንደሚሸቃቅጡት እንደ ብዙዎቹ አይደለንምና፤ በቅንነት ግን ከእግዚአብሔር እንደ ተላክን በእግዚአብሔር ፊት በክርስቶስ ሆነን እንናገራለን፡፡» ***ካል ቆሮ 2፡15-17፡፡***
- ቅዱሳን ራሳቸውን ሳይሆን ክርስቶስን የሚያሳዩ መስተዋት ናቸው፡፡

## *ቅዱሳን  የተመረጡት ከሁሉም የሰው ደረጃ ነው*

- ‹‹ በእግዚአብሔር ለተወደዳችሁና ቅዱሳን ልትሆኑ ለተጠራችሁ በሮሜ ላላችሁት ሁሉ…» ***ሮሜ 1፡7፡፡***
- « በቆሮንቶስ ላለች ለእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን፥ በክርስቶስ ኢየሱስ ለተቀደሱት፥ የእነርሱና የእኛ ጌታ የሆነውን የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ስም በየስፍራው ከሚጠሩት ሁሉ ጋር ቅዱሳን ለመሆን ለተጠሩት…» ***ቀዳ ቆሮ 1፡2፡፡***
- ቅዱሳን ሰዎች ከሚገኙባቸው ከሁሉም ዓይነት ደረጃዎች የወጡ ናቸው፡፡
- ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በእያንዳንዱ ሰው መስሎ መታየት የሚገባው እንዴት እንደሆነ በሕይወታቸው ያስተምሩናል፡፡
- በንግድ፣ በሳይንስ፣ በተለያዩ ምድራዊ የሥራ መስኮች ተጠቃሽ ምሳሌ የሚሆኑ ሰዎች እንዳሉ ሁሉ የእምነታችንም ምስክሮች አሉን፡፡ እነርሱም ቅዱሳን ናቸው፡፡

# መግቢያ

- ወታደሮች፣ የሥነ ጽሑፍ ሊቃውንት፣ መሪዎች፣ መምህራን፣ የቤተሰብ ኃላፊ የሆኑ፣ በጸሎት የተጠመዱ፣ ሕሙማንን የመፈወስ ሀብት ያላቸው፣ በተለያየ የሥራ መስክ የተሠማሩ፣ ወዘተ ቅዱሳን በቤተክርስቲያን እናገኛለን፡፡

***ቅዱሳን ከሰው መካከል የተገኙ ናቸው***

- ቅዱሳን እንደኛ ሰው ሆነው በሕይወታቸውና በሥራቸው እግዚአብሔርን ደስ በማሰኘት የተመረጡ ናቸው፡፡
- ቅዱሳን በዚህ ዓለም በኖሩበት ዘመን ተስፋ የሚያስቆርጥ ሁኔታ እየገጠማቸው አልፈውታል፡፡
- ‹‹ከጥቂት ቀንም በኋላ ጳውሎስ በርናባስን፡፡ ተመልሰን የጌታን ቃል በተናገርንበት በየከተማው ሁሉ ወንድሞችን እንጐብኛቸው፥ እንዴት እንዳሉም እንወቅ አለው፡፡ በርናባስም ማርቆስ የተባለውን ዮሐንስን ደግሞ ከእነርሱ ጋር ይወስድ ዘንድ አሰበ፤ ጳውሎስ ግን ይህን ከእነርሱ ጋር ሊወስድ አልፈቀደም፥ ከእነርሱ ዘንድ ከጵንፍልያ ተለይቶ ነበርና፥ ወደ ሥራም ከእነርሱ ጋር አልመጣም ነበርና፡፡ ስለዚህም እርስ በርሳቸው እስኪለያዩ ድረስ መከፋፋት ሆነ፥ በርናባስም ማርቆስን ይዞ በመርከብ ወደ ቆጵሮስ ሄደ፡፡…» ***የሐ ሥራ 15፡36-39፡፡***
- በበርናባስና በጳውሎስ መካከል የነበረው አለመግባባት በተለያየ አቅጣጫ ለመንዝ አግባብቶአቸው ነበር፡፡
- ቅዱስ ጳውሎስ ይኸንኑ በማስታወስ ለቆሮንቶስ ሰዎች «… ከእናንተም አንዳንዶቹ እንደ እነዚህ ነበራችሁ፤ ነገር ግን በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም በአምላካችንም መንፈስ ታጥባችኋል፥ ተቀድሳችኋል፥ ጸድቃችኋል፡፡» ***ቀዳ ቆሮ 6፡11፡፡***
- ከነበረባቸው ድካም መርጦ አበርትቶ የሰው የሆነው ድካም አርቆ የራሱ መሳሪያዎች ያደረጋቸው አምላካችን የተመሰገነ ይሁን፡፡

# መግቢያ

***ቅዱሳን የእግዚአብሔር ቤተሰቦች ናቸው***

- ቅዱስ ጳውሎስ ለኤፌሶን ሰዎች በጻፈው መልዕክቱ ‹‹እንግዲያስ ከእንግዲህ ወዲህ ከቅዱሳን ጋር ባላገሮችና የእግዚአብሔር ቤተ ሰዎች ናችሁ እንጂ እንግዶችና መጻተኞች አይደላችሁም፡፡» ኤፌ 2፡19፡፡ በማለት ጽፎልናል፡፡

***ቅዱሳን የእምነታችን አርበኞች ወይም ምስክሮች ናቸው***

- «እንግዲህ እነዚህን የሚያህሉ ምስክሮች እንደ ደመና በዙሪያችን ካሉልን፥ እኛ ደግሞ ሸክምን ሁሉ ቶሎም የሚከበንን
  ኃጢአት አስወግደን፥ የእምነታችንንም ራስና ፈጻሚውን ኢየሱስን ተመልክተን፥ በፊታችን ያለውን ሩጫ በትዕግሥት
  እንሩጥ፤ እርሱ ነውርን ንቆ በፊቱም ስላለው ደስታ በመስቀል ታግሦ በእግዚአብሔር ዙፋን ቀኝ ተቀምጦአልና፡፡
- የኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ግድግዳዎች በነዚህ ቅዱሳን የምስክርነት ሥራ የተሞሉ ናቸው፡፡
- ቅዱሳን ዛሬ በጉዞ ላይ ላለነው ሁሉ የሚያስተምሩት ምሳሌነት አላቸው፡፡
- አብርሃም፣ ኢዮብ፣ ነቢዩ ሙሴ፣ ነቢዩ ዳዊት፣ ነቢዩ ዳንኤል፣ ኢሳይያስ፣ ኤርምያስ፣ ማቴዎስ፣ ማርቆስ፣ ሉቃስ፣ ዮሐንስ፣ ቅዱስ ጊዮርጊስ፣ … ብዙዎቹ ሌሎቹም ቅዱሳን … ሁሉ እግዚአብሔር ያደረገላቸውን፣ አምላካቸውን እንዴት እንዳገኙት፣ እንዴት ያለ ጸጋና ሀብት እንደታደሉ ሁሉ ያለመሰወር ያስረዱናል፡፡

# መግቢያ

***ስለ ቅዱሳን በቅዱስ መጽሐፍ ብዙ ትምህርቶች ይገኛሉ***

- በመረጡት የቅድስና ጎዳና ስለሚገጥማቸው ‹‹የባሪያዎችህንም በድኖች ለሰማይ ወፎች መብል አደረጉ፥ የጻድቃንህንም ሥጋ ለምድር አራዊት ደማቸውንም በኢየሩሳሌም ዙሪያ እንደ ውኃ አፈሰሱ፥ የሚቀብራቸውም አጡ፡፡» ***መዝ 78፡2-3፡፡***
- የሰው ወገንም ለእግዚአብሔር ቅዱሳን ክብር እንዲሰጥ በማስጠንቀቅ «በድፍረትና በትዕቢት በመናቅም በጻድቅ ላይ የሚናገሩ የሽንገላ ከንፈሮች ድዳ ይሁኑ፡፡» ***መዝ 31፡18***
- ስለ ቅዱሳንም ያደረግነውን አስመልክቶ «እግዚአብሔር፥ ቅዱሳንን ስላገለገላችሁ እስከ አሁንም ስለምታገለግሉአቸው፥ ያደረጋችሁትን ሥራ ለስሙም ያሳያችሁትን ፍቅር ይረሳ ዘንድ ዓመፀኛ አይደለምና፡፡» ዕብ 6፡1፡፡ በማለት አሳስቦናል፡፡
- መታሰቢያቸውንም አስመልክቶ «ለዘላለም አይናወጥም የጻድቅ መታሰቢያ ለዘላለም ይኖራል፡፡» ***መዝ 111፡6*** ፣ «የጻድቅ መታሰቢያ ለበረከት ነው የኃጥኣን ስም ግን ይጠፋል፡፡» ***ምሳሌ 10፡7*** ፣ «ጻድቅንም በጻድቅ ስም የሚቀበል የጻድቁን ዋጋ ይወስዳል፡፡» ***ማቴ 10፡40፡፡***
- ከነዚህ ቅዱሳን የምትልቀው፣ ቅዱሳን ሰዎችንና አገልጋዮቹ ንጹሐን መላዕክትን የቀደሳቸው ቅዱስ አምላካችንን ዙፋን ሆና በማኅፀንዋ የተሸከመችው ቅድስተ ቅዱሳን እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ናት፡፡
- ለሚቀጥሉት ጥቂት ሳምንታት የምንማረው ስለ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ነው፡፡
- እመቤታችን የአምላካችን እናት ስትሆን በጸና እምነት ለተገኙትም እናት ሆና ስለተሰጠች - ይህንኑ የሚዳስስ በቂ ዕውቀት መጨበጥ ከስህተት ከመጠበቁም በላይ የሳተውን ለማረምና ለሕይወት ወደ ጀመርነው ጉዞ በእውነት ብቻ እንድንራመድ ያግዛል፡፡

For your queries or questions E-mail:
kesisolomon4@gmail.com

To get all the lessons, surf :
www.zeorthodox.org

# ወስብሐት ለእግዚአብሔር።